## የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**መግቢያ፡**

**አገራችን ኢትዮጵያ፤ ህዝቧ ባለፉት አርባ ዓመታት ውስጥ ሶስት አምባገነንና ጨቋኝ መንግሥታትን ለማስወግድና ዴሞክራሲን አስፍኖ የሥልጣኑ ባለቤት ለመሆን ያደረገው ትግል የብዙ መውደቅና መነሳት ሰለባ ከመሆን ለማለፍ ሳይችል ቀርቶ፤ ዛሬም ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ ስርዓት የተንሰራፋባትና መሰረታዊ የስብዓዊ መብቶች የተገፈፉባት፣ ዜጎች በእኩል የማይታዩባት፣ በዘርና በጎሳ እንዲከፋፈሉ የተደረገባትና አንድነቷ አደጋ ላይ የተጣለበት፣ የወደቀበት መሆኗን በማጤን፣ ይሕንን አፋኝና አምባገነናዊ ስርዓት አስወግዶ በህገ-መንግስታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመተካት የተባበረ ትግል እንደሚያ ስፈልግ በማመን፤**

- በኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት፤ የሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነትና ሉዑላዊነት ጽኑ ዕምነት ያላቸው፣
- ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች በህግ ፊት እኩል መሆናቸዉን የተቀበሉ፣
- ፍትኀ በሰፈነበትና የህግ የበላይነት የተረጋገጠበት ሥርዓት አስፈላጊነት የሚያምኑ፣
- በድርጅቶች ውስጥና መሃከል ዴሞክራሲያዊነትን መመሪያ ያደረጉና በሥራ የሚያውሉ፣
- በስልጣን ላይ የሚገኘው የህወሓት/ኢህአደግ አገዛዝ ለዴሞክራሲ መስፈንና ለብልጽግና እንቅፋት የሆነ ስርዓት በመሆኑ መወገድ እንዳለበት የተቀበሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪል ማህበራትና በርካታ አገር ወዳድ ግለሰቦች ከግንቦት 10 እስከ ግንቦት 13 . 2004 ዓ.ም በካናዳ ባደረጉት ጉባኤ በጋራ ለመታገል ወስነዋል። በዚህም ውሳኔ መሰረት፤

አንቀጽ 1. <u>**የጋራ ትግሉ ስብስብ መጠሪያ ፦**</u>
የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ ወይንም በአጭሩ (ሸንጎ)

አንቀጽ 2. <u>**አርማ**</u>

አርማው በዘንባባ የተከበበ፣ በሕዝብ እጅ የተደገፈ ጋሻ፤ መደቡ የኢትዮጵያ ሰንድቅ ዓላማ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ

አንቀጽ 3. <u>**ዓላማና ተግባር**</u>

**3.1 አላማ**

3.1.1 በቀጣይ ውይይትና ድርድር ሁሉም ኢትዮጵያውያን የዴሞክራሲና የአንድነት ሃይሎች በአንድነት እንዲመጡና ትግላቸውን እንዲያስተባብሩ ማድረግ። ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ስለሚከበሩባት፤ ዜጎች በእኩልነት፤ በመፈቃቀድና በመተሳሰብ አብረዉ ስለሚኖሩባት፤ ሀገራዊ አንድነቷ ስለሚረጋገጥባት፤ የብሄሮች ባህልና ቋንቋዎች ስለሚከበሩባትና ስለሚበለጽጉባት፤ የእምነት ነጻነት ስለሚከበርባት፣ የመድበለ ፓርቲ የፖለቲካ ሥርዓትና ተሳትፎ ዕውን ስለሚሆንባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያና ህዝብም የስልጣን ምንጭና ባለቤት ስለመሆኑ የሕሊና ንቃቱ ከፍ እንዲል በማድረግ የተቃዋሚውን አቅም ማጠናከር

3.1.2 በተባበረ ሕዝባዊ ትግል አምባገነኑን አገዛዝ ማስወገድ።

3.1.3 ለዴሞክራሲ፤ ለፍትህና ለነጻነት በሚደረገው ትግል የተካፈሉ፤ በአገር ቤትና ውጭ ያሉ ሁሉም የፖለቲካና ሲቪክ ማህበራት፣ ጉልህ አስተቃጽዖ ያደረጉ ታዋቂ ግለሰቦችና የማህበረሰብ መሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ተወካዮች በሚሳተፉበት ብሄራዊ ጉባኤ ከ2 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ብቻ የሚቆይ የሽግግር መንግሥት መመስረት፤ በነጻ የሕዝብን ተሳትፎ ድጋፍን ያገኘ ሕገ-መንግሥት እንዲጸድቅ ማድረጋና በሕገ-መንግሥቱ መሠረት በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ለሚመረጥ መንግሥት ሥልጠንን ማስረከብ

## 3.2 ተግባር

3.2.1 በ3.1.2 የተቀመጠው ከሁሉም በፊት መደረስ ያለበት ቁልፍ ዓላማ ስለሆነ፣ ከተቃራኒው በኩል የሚሰነዘረውን ጥቃት የሚቋቋም አጸፋ ለመስጠት የሚያስችል ሕዝባዊ ሃይልን ማደራጀት፣

3.2.2 የትግሉ ወና መናኸሪያ በሃገር ውስጥ መሆኑ ተሰምሮበት፣ በውጭ የሚደረገው መደራጀትም ሆነ ትግል ለውስጡ ድጋፍ መሆኑ ሳይዘነጋ፣ በሐገር ቤት ሕዝብ ተደራጅቶ ሊንቀሳቀስ የሚችልበትን አቅጣጫ ለመቀየስ፣ በቅድሚያ በሀገር ውስጥ ከሚገኙ የተደራጁም ሆኑ ያልተደራጁ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ጋር ግንኙነት በመፍጠርና በህጋዊም ሆነ በሕቡዕ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች አጥንቶ አስፈ ላጊውን ማድረግ፣

3.2.3 ስለትግሉ ዓይነት አወሳሰን፣ በአንቀጽ 3.2.1 የተቀመጠው እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ የሸንጎ የአማራጮች ሁሉ አማራጭ የሚሆነው፣ ጨቋኝም ተጨቋኝም፣ ተቃዋሚም ደጋፊም፣ የመስሚያ ጆሯቸው ተከ ፍቶ፣ የማስተዋል ሕሊናቸው በርቶ፣ ለሚያለያያቸው ሳይሆን ለሚያስተባብራቸው ጉዳይ ቅድሚያ ሰጥተው በጋራ ከሚያደርጉት ውይይት ለሚገኝ ውጤት መሆኑን ያሰምርበታል።

3.2.4 ትግሉን ከሌሎች ጋር ማቀናጀት፣

1) በሸነጎው ያልታቀፉና ሥርዓቱን ለማስወገድ ትግል ከሚያደረጉ ሌሎች ስብስቦች ጋር ከሸንጎው የመርህና የአላማ ነጥቦች ያልራቁ እስከሆኑ ድረስ ትብብር ማድረግ፣ ከሸንጎው ዋና ዋና ተግባረቱ አንዱ ሲሆን፣

2) እያንዳንዱ ድረጅት ስለሚከተለው የትግል ዘዴም ሆነ፣ ዓይነት ለውጤት ያበቃኛል የሚለውን የሸንጎውን ዓላማ እካተጻረረ ድረስ የመምረጥ መብቱ የተጠበቀ እንደሆነም ያምናል ይቀበላልም።

3.2.5 የጋራ ትግሉ አድማስ የሚሰፋበትን፣ የውጭና የውስጡ የሚተሳሰሩበትን አጠቃለይ አቅጣጫ ማሳየትና፣ ለተግባራዊነታቸው መሥራት፣

3.2.6 ከልዩ ልዩ መነግሥታትና አለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት መፍጠር፣ በኢትዮጵያ ለፍትህ፣ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ለሚደረገው ትግል የፖሊካና የድፕሎማሲ ድጋፍ ለማስግኘት መሥራት፣

<u>የሸንጎ መስራች አበላት</u>

| <u>ሀ. የፖለቲካ ድርጅቶች</u> | <u>ስም</u> | <u>ፊርማ</u> |
|---|---|---|
| 1. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ሕብረት | ............................... | ................................... |
| 2. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓረቲ ዲሞክራት | ............................... | ................................... |
| 3. ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር | ............................... | ................................... |
| 4. ትንሳኤ ኢትዮጵያ የአርበኞች ሕብረት | ............................... | ................................... |
| 5. ታጠቅ ለነጻይቱ ኢትዮ. ዴሞክ. አንድነት ንቅናቄ | ............................... | ................................... |
| 5. የኢትዮጵያ መድህን ዴሞክራሲያዊ ፓረቲ (መድህን) | ............................... | ................................... |
| <u>ለ. ሕዝባዊ ድርጅቶች</u> | | |
| 6. የኢትዮጵያ ፖለቲካ አስረኞች አነድነት ኮሚቴ በካናዳ | ............................... | ................................... |
| 7. የኢትዮጵያ የሲቪክ ማሕበራት ስብስብ በ እንገሊዝ አገር | ............................... | ................................... |
| 8. ኢትዮ ካናዳ የዴሞክራሲ መድርክ | ............................... | ................................... |
| 9. የኢትዮጵያውያን የግራ መድረክ ኖረዌይ | ............................... | ................................... |
| 10. የዳላስ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ኮሚቴ | ............................... | ................................... |
| 11. በዋሽንግተን ዲሲ በተካሄደው የሸንጎው 2ኛ ጉባዔ ተሻሽሎ የጸደቀ | | |

ቀን 05.07.2013 ዓ.ም.

*Tel .:* +44 7937600756 , +1 9168486790
*E-mail :* shengo.derbiaber@gmail.com